# የውጭ ጣልቃ ገብነትን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ጠንካራ የውጭ ግንኙነት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በሀገራት መካከል የሚደረግ ግንኙነት የዓለምን ሰላም ለማስከበር፣ በሀገራት መካከል መልካም ግንኙነትን ለማጎልበት፣ ዓለማቀፋዊ ትብብርን ለማጠናከር ይረዳል፡፡ በረዥሙ የመንግሥትነት ታሪኳ፣ ሀገራችን በውጭ ግንኙነት ዘርፍም የረዥም ጊዜ ልምድ እና ሰፊ ተሞክሮ ባለቤት ናት፡፡ ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ፣ ከእስያ እና ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር የረዥም ጊዜ የዲፕሎማሲ ታሪክ አላት፡፡ ነፃነቷን አስጠብቃ የኖረችው ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ በተለያዩ ወቅቶች ሉአላዊነቷን የሚፈታተኑ ልዩ ልዩ የውጭ ጫናዎች እና ጣልቃ ገብነቶች አጋጥመዋታል፡፡ በመሆኑም የሀገራችን የውጭ ግንኙነት ታሪክ በስኬቶች እና ተግዳሮቶች የተሞላ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አንዳንድ የጎረቤት ሀገራት እና በሩቅ የሚገኙ የአውሮፓ እና የአሜሪካ መንግስታት በኢትዮጵያ ላይ እያደረሱት ያለው ጫና እየጨመረ መጥቷል፡፡ በምዕራብ የሀገራችን ክፍል የሱዳን መንግስት ወታደሮች ድንበራችንን ጥሰው በመግባት መሬታችንን ወረዋል፣ ሕዝባችንን አፈናቅለዋል፡፡ በትግራይ ክልል የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ ድንበራችንን አቋርጠው የገቡ የኤርትራ ወታደሮች ግዛታቻንን ለቀው ስለመውጣታቸው እስከ አሁን ግልጽ መረጃ የለም፡፡ የግብጽ መንግስት በአባይ ወንዝ ላይ የመጠቀም ተፈጥሯዊ እና ህጋዊ መብታችንን በመካድ የታላቁን ህዳሴ ግድብ ግንባታ ለማስተጓጎል፣ ብሄራዊ ጥቅማችንን እና ሉአላዊነታችንን በመፈታተን ላይ ይገኛል፡፡

ከምዕራባውያን ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነትም እየሻከረ መጥቷል፡፡ የአውሮፓ ህብረት 6ኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ለመታዘብ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሉአላዊነታችንን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ሆነው መገኘታቸውን መንግስት አስታውቋል፡፡ በአንጻሩ የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ የቪዛ እገዳ ከመጣሉ ባሻገር ከሰብአዊ ድጋፍ ውጪ ያሉ ኢኮኖሚያዊ እና የደህንነት ድጋፎችን እንደሚያቋርጥ አስታውቋል፡፡ የአሜሪካ መንግስት ተጨማሪ ማዕቀቦችን ሊጥል እንደሚችልም ገልጿል፡፡

የውጭ ሀገራት ኢትዮጵያን አስመልክቶ ለወሰዷቸው እርምጃዎች የተለያዩ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የንጹሐን ሞት፣ የፖለቲካ እስረኞች መኖር፣ የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ፣ ዓለም አቀፍ የምርጫ መመዘኛዎች አለመሟላት ከብዙ በጥቂቱ ይገኙባቸዋል፡፡

**የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት** የውጭ ኃይላት የሀገራችንን ሉአላዊነት እና ብሄራዊ ጥቅማችንን የሚሸራርፉ፣ ከዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ያፈነገጡ አድሏዊ እና ኢ-ፍትሀዊ ውሳኔዎችን አጥብቆ ይቃወማል፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የሀገራችን ዓለም አቀፍ ግንኙነት እንዲጠናከር፣ ሀገራችን በዲፕሎማሲው መስክ ያላት ሚና እና ተሰሚነት እንዲጎለብት፣ በተለይ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነት ይበልጥ መጠናከር አለበት ብሎ ያምናል፡፡ የጋራ ምክር ቤታችን የሀገሮች ሉአላዊነት ሳይሸራረፉ እንዲጠበቁ እና በሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንዲቆም መንግስታት የገቧቸውን ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ሊያከብሩ ይገባል ብሎ ያምናል፡፡

**የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት** ሀገራችን ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገር መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ያላት ግንኙነት እንዲሻሻል፣ አድማሱ በፍጥነት እየሰፋ በመጣው ሉላዊነት (globalization) ውስጥ የሀገራችንን ጥቅም በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ፣ የበለጸጉ ኃያላን መንግስታት የሚደርሱብንን ኢ-ፍትሀዊ ጫናዎች በተባበረ ክንድ ለመመከት እንድንችል በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በዜጎች እና በሌሎች አካላት የሚከተሉት ስራዎች ሊሰሩ ይገባል ብሎ ያምናል፣

1. ኢትዮጵያውያን ሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት ያጋጠሟትን ፈተናዎች እና የውጭ ጣልቃ ገብነቶች በአንድነት በመቆም የውጭ ኃይላት ጫና መክተናል፡፡ በዚህ ሂደት በተለይም የሀገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጣዊ ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን በመተው ለሀገር ሉአላዊነት መከበር በአንድነት ታግለዋል፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አመራሮች ይህንን አኩሪ ታሪካችንን ዛሬም ይበልጥ አጠናክረን በውጭ ግንኙነታችን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመከላከል እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነት መቆማችንን እናረጋግጣለን፣

2. የውጭ ኃይላት ሁሌም በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ የሚገቡት እና የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚፈታተኑት አንድነታችን ሲላላ እና የውስጥ ሰላማችን ሲዳከም መሆኑ በተለያዩ ወቅቶች ታይቷል፡፡ በመሆኑም በሉአላዊነታችን እና በብሄራዊ ጥቅማችን ላይ የተደቀኑ የውጭ ኃይላትን ሴራ እና ዛቻ ለመቋቋም የውስጥ ሰላማችንን መጠበቅ፣ ብሄራዊ መግባባትን መፍጠር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን የጋራ ምክር ቤታችን በጽኑ ያምናል፡፡ በመሆኑም በተለይ መንግስት ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በጋር እና በትብብር እንዲሰራ ጥሪ እናቀርባለን፣

3. የውጭ ሀገራት በተለይም የአውሮፓ እና የአሜሪካ መንግስታት ሀገራችንን አስመልክቶ ለወሰዱት አቋም እንደ ምክንያት ያቀረቧቸው የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብት፣ የብሄራዊ መግባባት፣ የኤርትራ ወታደሮች ከኢትዮጵያ መውጣት እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ከውጭ መንግስታት ይልቅ የኢትዮጵያን ህዝብ እና የፖለቲካ ኃይሎችን የሚመለከቱት ናቸው፡፡ እነዚህ የውስጥ ጉዳዮቻችን ሊፈቱ የሚገባው በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በሀገራችን ህዝብ ተሳትፎ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም በተለይም መንግስት የውጭ ኃይላት በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ ለመግባት እንደ ምክንያት የሚደረድሯቸው ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች እንዲፈቱ ብሄራዊ እርቅ እና ውይይት እንዲካሄድ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ እንጠይቃለን፣

4. ባለፉት ጥቂት ሳምንታት የውጭ ኃይሎች ሀገራችንን አስመልክቶ የወሰዷቸው ውሳኔዎች ግልጽነት እና ቅንነት የጎደሏቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ የቪዛ ክልከላ ለማድረግ የኤርትራ ወታደሮች ኢትዮጵያን ለቀው መውጣትን እንደ ምክንያት የወሰደው የአሜሪካ መንግስት፣ ሀገራችንን በኃይል ወሮ የያዘውን የሱዳን መንግስት አስመልክቶ የገለጸው አቋም የለም፡፡ የበለጸጉ ሀገራት የራሳቸውን ብሄራዊ ጥቅም ለማስከበር አለማቀፍ ስምምነቶችን ተላልፈውም ቢሆን በተለይም በታዳጊ የአፍሪካ ሀገራት የውስጥ ጉዳይ የመግባት ረዥም ታሪክ

እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ **የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት** ለዓለም አቀፍ ስምምነቶች መከበር ቆመናል የሚሉ ሀገራት በሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም ላይ የሚያሳዩትን ኢፍትሀዊ አሰራር ቆም ብለው እንዲፈትሹ ያሳስባል፣

5. በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በብሄራዊ ጥቅማችን እና ሉአላዊነታችን ላይ የሚቃጡ ጫናዎችን ለመቋቋም ሁሌም ስታደርጉ እንደቆያችሁት ከሀገራችሁ እና ከወገናችሁ ጎን በመቆም ሀገራችን ከየአቅጣጫው የተጋረጡባትን የውጭ ግፊቶች ለመቋቋም የፖለቲካ እና ሌሎች ልዩነቶችን ተሻግራችሁ በጋራ እንድትሰሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን፣

6. ኢትዮጵያ ከበርካታ የአውሮፓ እና የአሜሪካ መንግስታት ጋር የረዥም ጊዜ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት፡፡ ይህ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት ካለው ጠቀሜታ ባሻገር በአፍሪካ በተለይም ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም እና መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው፡፡ ኢትዮጵያ በተለይ በአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ያላት ሚና ከፍተኛ ሲሆን ሀገራችን ያላት ከፍተኛ ጂኦ ፖለቲካዊ አቅም ከበርካታ ሀገራት በሰላም እና ደህንነት እንዲሁም ሌሎች አለም አቀፍ ጉዳዮች ጠንካራ አጋር ሆና እንድትመረጥ አድርጓታል፡፡ ይህንን ከፍተኛ አቅም ይበልጥ በማጎልበት ለሀገራችን ጥቅም እንዲውል ለማድረግ መንግስት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ ሊሰራ ይገባል፣

7. ህዝባችን ከከፉ ድህነት ተላቅቆ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል እየጣረች ያለችው ሀገራችን ከውጪው ዓለም በተለይም ከበለጸጉ ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት ልትፈጥር፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ባህላዊ ትስስርን ልታጠናክር ግድ ይላታል፡፡ ባለንበት ፈጣን የኢኮኖሚ እና የንግድ ግንኙነት ዘመን ከጎረቤት ሀገራትም ሆነ ከቀሪው ዓለም ጋር ጠንካራ ምጣኔ ሀብታዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህን ከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ጠንካራ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ፣ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ እና ብቁ አመራር ይጠይቃል፡፡ ባለፉት ረዥም ዘመናት መንግስት ለውጭ ግንኙነት ዘርፍ የሰጠው ዝቅተኛ ትኩረት አሁን ላገጠሙን የውጭ ጫናዎች እንደ ምክንያት አገልግለዋል፡፡ በመሆኑም እንደ ሀገር ለውጭ ግንኙነት ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጥ፣ የዲፕሎማቶቻችን የማስፈጸም አቅም እንዲጎለብት መንግስት በቂ ትኩረት እንዲሰጥ የጋራ ምክር ቤታችን ያሳስባል፣

8. የህዳሴው ግድብ ኢትዮጵያውያን ከድህነት ለመላቀቅ የሚያደርጉትን የሞት ሽረት ትግል ዳር ለማድረስ ትልቅ ተስፋ የተጣለበት የዚህ ትውልድ ታላቅ ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህ ታላቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ዛሬ ላይ የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ መላው የሀገራችን ህዝብ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን እና ህይወታቸን ጨምር ገብረዋል፣ ወደፊትም ተጨማሪ ድጋፍ ለማድረግ ቁርጠኝነታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ የታላቁ ህዳሴ ግድብ በተፈጥሮ ሀብታችን የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብታችን ማረጋገጫ ፕሮጀክት ነው፡፡ የግድቡን ቀሪ ግንባታም ሆነ ሁለተኛ ዙር የውሀ ሙሊት ለማስተጓጎል በየትኛውም አካል የሚደረግ  ጥረት የሀገርን ሉአላዊነት ከመሸራረፍ ተለይቶ አይታይም፡፡ በመሆኑም የግድቡን ግንባታ ለማጠናቀቅ መላው የሀገራችን ህዝብ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን፣

9. በትግራይ ክልል በተከሰተው ግጭት ሳቢያ በሰላማዊ ዜጎቻችን ላይ የደረሰው ሰብአዊ ጉዳት የመላው ኢትዮጵያውያን ጉዳት ነው፡፡ በመሆኑም በንጹሀን ዜጎች ላይ የደረሰ የህይወት እና የንብረት ጉዳታ በገለልተኛ አካላት ተጣርቶ ጥፋተኞች ለፍርድ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር - መንግስት የጀመረውን ስራ በፍጥነት አጠናቆ ጥፋተኞችን ለፍርድ እንዲያቀርብ፣ በጦርነቱ ለተጉዱ ዜጎች በቂ ሰብአዊ ድጋፍ እና በዘላቂነት የሚቋቋሙበትን የመልሶ ማቋቋም ስራ እንዲሰራ የጋራ ምክር ቤቱ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በትግራይ ክልል የተፈጠረው ሰብአዊ ቀውስ ከውጭ ኃይሎች ይልቅ የኢትዮጵያውያን ቁልፍ አጀንዳ ሊሆን ይገባል፡፡ ያለንን ሙሉ አቅም ተጠቅመን በትግራይ ክልል የደረሰውን ሰብአዊ ቀውስ ለማስቆም መላው የሀገራችን ህዝቦች በጋራ ልንሰራ ይገባል፡፡ የትግራይ ክልል ችግር  ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ምክንያት መሆኑ በአስቸኳይ እንዲቆም ለማድረግ በተለይም የክልሉ ጊዚያዊ አስተዳደር እና የፌዴራል መንግስት አስፈላጊው ሁሉ እንዲያደርጉ እናሳስባለን፣

10. ጠንካራ የአለም አቀፍ ግንኙነት ከድህነት ለመላቀቅ የምናደርገውን የውስጥ ጥረት ለማገዝ የሚረዳ ጠንካራ የፖለቲካ መሳሪያ ነው፡፡ በሁሉም መስክ የተሳካ የውጭ ግንኙነት ስራ ለመስራት ለዘርፉ በቂ ትኩረት እና ክብር መስጠት፣ በቂ እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማዘጋጀት እና ማሰማራት ይፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በተለይም ከፍተኛ የፌዴራል እና የክልል የመንግስት ኃላፊዎች ጉዳዩን አሳንሶ እና አቅልሎ ከመመልከት አባዜ ወጥተው ኢትዮጵያን እና ክብሯን የሚመጥን የዲፕሎማሲ ቋንቋ ሊጠቀሙ እና ተመጣጣኝ ስራ ሊሰሩ እንደሚገባ ምክር ቤታችን ያስገነዝባል፣

11. በመጨረሻም ምርጫ ከአንድ ሀገር የሉአላዊነት መገለጫዎች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ምርጫ 2013ን ለማካሄድ የመጨረሻ ምእራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ምርጫው የሀገራችን ህዝቦች የሚፈልጉትን መሪ በነጻነት በድምጻቸው መርጠው ሀገራችንን ካላችበት ውስብስብ የውስጥ እና የውጭ ችግሮች ሊያላቅቅ የሚችል ጠንካራ መንግስት እንዲመሰርቱ እድል ይፈጥራል፡፡ ይሁን እንጂ የሀገራችን ሰላም እና ብልጽግና የማያስደስታቸው ኃይላት ምርጫው በሰላም እንዳይካሄድ የተለያዩ ሙከራዎችን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ በመሆኑም መላው የሀገራችን ህዝብ ምርጫው ከማናቸውም የውጭ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆኖ እንዲካሄድ የበኩላችሁን እንድትወጡ የጋራ ምክር ቤታችን ጥሪውን ያቀርባል፣

**የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት**

**ሰኔ 4 2013**

**አዲስ አበባ**

Politicalparties.et@gmail.com
ቦሌ የሺ ህንፃ 7ኛ ፎቅ ፤ አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ   Bole Yeshi building 7th floor, Addis Ababa, Ethiopia